## ጀግና ሰው የት ገባ?

ሀማ ቱማ

ሳናረጅ ሳንጃጃ ታሪክን ሳንረሳ
ማየት ሳያቅተን ዓይናችን ሳይጠፋ
ነግ የሚወሳውን ትላንትና ኖረን
በእንባችንም ወንዝ በደም ቀይ ባህር ላይ
የታሪክን ጀልባ ወደ ግራ ቀዝፈን
ከሕዝብ ወደብ ከተን
ሞት ለግራዚያኒ የአርበኞች መፈክር
በወጣት ቁጡዎች በታሪክ ወራሾች ሲጎሰም ትላንትም
ገድለን ፍርሀትን፣ ያን ራስ መውደድን
ለምትጮህ ሀገር አለና እያልን
በፃረሞት ስቀን በመሀይም መንጋ በነፍሰ ገዳዩ አሹፈን አላግጠን
ሞት አይፈሬ ትወልድ የፋሺስት መጋኛ
ሀገር ወዳድ ትውልድ የጠባብ ማርከሻ
ሽቶ ከርቤ ቀርቶ ባሩዱን ታጥኖ
በወግ ቀብሩ ሲተን መንገድ መጣል ደርቶ
የሞት ፅዋን ጨላጭ በመዝሙር አጅቦ
በእናቸንፋለን ጥይትን ከልሶ
ማን ይፈራል ሞትን ክታቡ ያረገው
ያ ትውልድ እንጂማ ሌላማ ሌላ ነው፡፡

ጳሮን ገዳይ ጨካኝ ሽብራቸው ክፉ
ስርዓቱ አረመኔ ልክ--አልባ የግፉ
ያ የነበር ጊዜ ገና ሳይረሳ
ያ ሁሉ ሰማዕት ገና ሳይዘከር
ከጋራ ጉድጓዱ ከምስጢር መቃብር
የጭቁኑ አጥንት ተቆፍሮ ሳይወጣ
ሳናረጅ ሳንጃጃ ታሪክን ሳንረሳ
ማየት ሳያቅተን ዓይናችን ሳይጠፋ
ህሊናችን በሆድ ታንቆ ሳይገደል
አሁን ምን አመጣው ያልነበረን ነበር ብሎ ለማሳመን
ደፋ ቀና ማለት ሌት ተቀን መባከን?
ወረቀት መጨረስ በዘረኛው ማጀት ሀሰትን መታጠን?

ያ የወልቃይት መሬት ጀግና የሞተለት፣ ጀግና የሞተበት
ያ የቋራ መሬት  ጀግና የበቀለበት፣ ጀግና የታገለበት
ያ የጎንደር መሬት፣ ያ የወሎ መሬት፣  የኢትዮጵያ መሬት
ጀግና ሰው ጠፍቶ ነው ሱዳን የገባበት?
ጀግና ሰው ጠፍቶ ነው ወያኔ ያዘዘበት?

ድንጋይ ዳቦን ዘመን መች እኛ አየነው፣
ነጋ ጠባ ርሀብን ሁሌ እየታቀፍነው።
ሶሰቴ ማዕድ በቀን ቃል ኪዳን ገቡልን
ታስቦ ራት ይቆይ በጦም ሊያሳድሩን።
ግና
የኮለኔል ሽብር በቁማችን ገሎን
ለጠባቡ መንጋ ማጎብደዱ ቀሎን
ጫንቃችን ለሸክም አለና እያሰኘ ሳናውቅ ኖሮ ገድሎን።
ታሪክ ዋሽቶ ጠፋ ትውልድ ቆመጠጠ
ነበረ ነበረን እየደጋጋመ ?
ወይስ
ትላንት ዛሬ ልዩ ሰማይና መሬት?
ለሀገር መሞት መስዋዕት ተብሎ ፋራነት
ብልጡ ዛሬ ፈልቶ የዲቪ አርበኛ
ፖለቲካው ቡርቅቅ ለጠባብ ዘረኛ
ኢንጂኔር ዶክተሩ የዕውቀት መናኸሪያ
ፖለቲካው ጮሌ መርህ አልባ ጉዞ
ማጠፊያ ላይ ሳይደርስ ሁሌም እጥፍ ብሎ
የሚካድ መርህም በዚህ በዚያው ጠፍቶ
ባንዳነት የቤት ልጅ ወገን መሸጥ ቆንጆ።
ክልል አንድ መወለድ የገነት በር ከፋች
ሰው በላ ጥርስ ለጋሽ ህሊናን አሚጣጭ
ሀገር ምን ሊፈይድ ክልል ሳለ ምቹ
እኛ ተበዝባዦች እነሱ ወርቆቹ።
እስከመቼ ታሪክ ተጨራምቶ ሊቆይ
እስከመቼ ሀገር መጫወቻ ልትሆን
ብሎ የሚጠይቅ  ምን ምላሽ ያገኛል
ዝምታ ነው መልሱ ወይስ ታሪክ ዋሽቷል?

''''''''''

የጋምቤላ መሬት ስንቱ የሞተለት
የቢሾፍቱው መሬት ስንቱ የወደቀለት
የኢትዮጵያ መሬት ደም የፈሰሰለት
ጠባቂ አጣ ዛሬ ቻይና ፈነጨበት
ህንዱና አረቡ ዝርፊያ አጧጧፈበት።

---

ድንጋይ ዳቦ ዘመን ያኔ ባላየነው
በዚያ ትውልድ ጊዜ አብረን በታገልነው
ቃልማ ቃል ነበር ሚዛኑ  የከበደ
ቃሌን አላጥፍ ብሎ ስንቱ ረገፈ ?
ሀገር ሀገር ብሎ ስንቱ ተቀጠፈ ?
የመደብ ልዩነት የሕይወትን ሚዛን ከባድ ቀላል አርጎ
የሕይወት ውድነት ለድሀው ተነፍጎ
መስዋዕትነቱ ክብር ቦታን ሲያጣ ማየቱ ተለምዶ
የኔው ብጤው ደሀ ለነሱው ጦርነት ሲማገድ ጧት ማታ
ሲሾም ሲሸላለም ፈርጣጩና ባንዳ
ላገር መሰዋቱ ሲነፈግ እውቅና
ጴጥሮስነት ከንቱ ከመሞት መበርከት
ለአላፊው አግዳሚው ሁል ጊዜም መንበርከክ
አለና ጫኑኝ ባይ ሀገር ወገን ካጂ
በፈላበት ሀገር ሙጃው እንክርዳዱ
ሰው በዪው አስበዪው ገራፊው ቆራጩ
ሽብርተኛው ፋሺስት ዘረኛው ጠባቡ
ዋ! ዝምታ ለበግም መች በጅቷት ያውቃል
እጅን ማጠፍ ከንቱ እጅን ያስቆርጣል
መጨመቱ ስህተት ባርነት ያመጣል
ቃታ ያልሳበም ጣት በስብሶ ይወድቃል።
ዋ!

---

ያ የሸዋ መሬት  ስንቱ የወደቀለት
የባሌ ሐረርጌ ፤  ያ የጅማ መሬት ደም የፈሰሰበት
ያ የአፋሩ መሬት ስንት ሰው የሞተለት
ዛሬ ሰው ጠፋና አረብ ጨፈረበት
ኮሪያው ጅቡቲው ባለቤት ሆነበት።

---

ግራዚያኑ ነጩ ሚሊዮን ሲገድል
ግራዚያኑ ጥቁር ብዙ ሺ ሲመትር
ጀግኖች ሲሰቀሉ ጀግኖች ሲገደሉ
ምድር ቀውጢ ሆና አመፅን አርግዛ
ጎህን ስትጠብቅ ብሩህ ቀን ሊመጣ
እናም በከተማው በመላ ሀገሩ
በዱር በገደሉ
ከጠባብ ከፋሺስት ጓዶች ሲዋደቁ
ፖለቲካ መድረክ ዛሬ አጣባቢዎች ከወዴት ነበሩ?
ጠባቦች በጋራ አድጊ አማራ ገዳይ ብለው ሲፎክሩ
በአሲምባ በወልቃይት በቋራ መተከል ጀግኖችን ሲገድሉ
ጠባቦች ሱዳኖች ግፍን ሲፈፅሙ ኢትዮጵያን ሲደፍሩ
አቶ ጋሼ ዶክተር ወደየት ነበሩ፤
እስቲ ለመመለስ ተነሱ ሞክሩ?
ትላንት ሀገር ገዳይ ትላንት ዜጋ ገዳይ
ትላንት ሀገር ገዢ ጨቋኝ ሕዝብ አሰቃይ
ጀግኖች አለቁ እንዴ ዛሬ አርበኛ ሲባል
ንስሃ ሳይገባ ፀፀትን ሳያሳይ?
ታሪክም ድንበርም ጠባቂ ሰው ካጣ
ጉድ በራሳችን ላይ ወዮላት ኢትዮጵያ!

---

ያ የከፋ መሬት የቡናው መብቀያ
የኢሉባቦር መሬት የዚያም የወለጋ
የሲዳሞ መሬት የሻኪሶው ወርቁ
የኢትዮጵያ መሬት አስጎምጂ ያ ለሙ
ባዕድ ጨፈረበት ዜጎቿ የት ገቡ?

---

ፎገራ ይቅርና ሽሮ ሜዳም ሰፋ
ዳሸን ላይታሰብ ደፍሮ ላይወጣ
ሀገር ማዳን ከባድ ህይወትን ጠያቂ
መከራና ስየል በደል አሸካሚ

ዘረባና ወሬ በገበያው ደርቶ
በአፍ ጦር ሰባቂዎች ድርጊት አፈር በልቶ
ሁሉም ሀፍረተ ቢስ ሁሉም ትችት አምራች
ሁሉም ትውልድ ወቃሽ ሁሉም ታሪክ ደምሳሽ
ሶሶት ሺው ተክዶ መቶ ዓመት ተባለ
የኔ ብጤው ደህ ጨቋኝ ተመሰለ
ያልነበረው ነበር ተብሎ ሲተረክ
የነበረው ሲካድ ሰማዕት ሲወገዝ
ትላንት የደም እጆች ዛሬ ርኩስ አፎች
ትላንት የደም እጆች ዛሬ ዋሾ ምስክሮች ፡፡
ጉልበትም ለትግል መሆኑ ቀረና
መንበርከክ መስገዱ የውርደት መውደቂያ ይሁን ተባለና
ሰው እርያ ሆነ መጨቅየትን መርጦ
እጆች ለጠመንጃ የሚል ጀግና ጠፍቶ፡፡
ያ ድንጋይ ዳቦ ዘመን ከቶም ያላየነው
በይመጣል ተስፋ በህልም እየኖርነው
እንክርዳዱ በዝቶ ሚወይን በርክቶ
ሀገር ጉድ መጣባት ማጭድ ታጋይ ጠፍቶ፡፡

ያ የጎጃም መሬት ስንቱ የወደቀለት
ያ አባይ ወንዛችን የተዘፈነለት
የግብፅ መጫወቻ መሆን ነበረበት?

አቡኑ ታጣቂ ቆንጆን አሸኮርማሚ
ሽማግሌው ጨቅላ የማይሆን መካሪ
ሀኪሙም ያው ጠንቋይ የምሁር አላዋቂ
አሳን በተራራ ሊያረባ ፈላጊ
ሰለባውም ደነዝ ሰላቢ አዳናቂ
ገዳይ ሀፍረተ ቢስ ሽልማት ፈላጊ
መጣና ድብልቅልቅ የጨረባ ተዝካር
ደልቅ ያን ከበሮ ለዘረኞቹ ዛር
ጨቋኝ ደም አፍሳሹ ጠባቡ ፋሺስቱ
ታሪክ ፃፊ ሆኖ ተረት ተረት ከንቱ
መስካሪ አስታዋሽ እየተባባሉ፡፡

የከህደት መደብር መደርደሪያው ሞልቶ
አዲስ ሰም ወጥቶለት ፓርላማና ሸንጎ
የወንበሩ ሽሚያ ክብር እየገፈፈ ፤ሰው እያቀለለ
                የቅሌቱም ክርፋት የፈረንሳይ ሽቶ ሆኖ እያባበለ
ስንቱ ተዋረደ ስንቱ ነሆለለ !
በሕዝብ ሰቆቃ ላይ ተራኳች በዛና፤ ተደሳች በዛና
ሀገር ቅርጫ ሻሞ በዴዎቹ መንጋ
አስመሳዩ ታጋይ  ሸፍንፍን ዘረኛ ዘመናዊ ባንዳ
ተምቾች እየፈሉ ሀገር እየበሉ ዜጋ እየገደሉ
የሳጥናዔል በረት የአውሬውና ጉዱ
ደደቢት አድዋ መንጋው የጠባበ
ሲርምሰምስ ባገር ሲቦጦቡጥ ሀገር ሲጨፍር ጧት ማታ
ተው የሚለው ጠፍቶ ቅጣት የሚቀጣ
የሚጠራ ጠፍቶ እጆች ለጠመንጃ
ጣቶችም አድመው አንስብ ብለው ቃታ
የጀግኖቹ ሀገር የሁሉ ኢትዮጵያ
ማን ሊሰማት ይሆን ስትሸጥ ለባዳ
ማን ሊያድናት ይሆን ስትጮህ ጠዋት ማታ?

የኢትዮጵያ መሬት ደም የፈሰሰለት
የኢትዮጵያ መሬት ጀግና የሞተለት
የት ሄደ ያገር ሕዝብ ጀግና ምን መጣበት
ለባንዳ ለባዕድ መጫወቻ መሆን ማነው ያዘዘበት?